**ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (ታህሳስ 6፣ 2000 ዓ. ም)**

## የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከፍተኛ የጦር መኮንኖችን በምስጢር በቤተመንግስት አነጋገረ

## ሌላም ዜና

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ጣቢያ

በሁሉም የሐገሪቱ ክፍሎች በሚገኙ የቀበሌ ገበሬ ማህበራት ውስጥ በየቀበሌው አንዳንድ ሥራ አስኪያጅ ለመመደብ እቅድ ተነድፎ በአንዳንድ አካባቢዎች ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን የገለፁት ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ቅርበት ያላቸው ምንጮች የሚመደቡት ስራ አስኪያጆች ሕዝቡ ያልመረጣቸው ፈፅሞ በአካባቢው ተወላጆች ያልሆኑ ነገር ግን ለብዙ ወራት የካድሬነት ትምህርት ሲሰጣቸው የነበሩ የወያኔ አባሎች መሆናቸውን የገለፁት ምንጮች እያንዳንዱ ተሿሚ የወያኔ ካድሬ ቋሚ ደመወዝ በወር ከ1700 ብር እስከ 2100 ብር ድረስ ተከፋይ ሲሆን፣ የሥራ ማስኬጃ በሚል ደግሞ ከ1000 ብር በላይ እንደተመደበላቸው አጋልጠዋል::

ሕዝቡ በመረጠው ይመራል እያሉ የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት በአደባባይ ቢለፍፉም ቃልና ተግባር መቼም ተገጣጥሞላቸው የማያውቁት ወያኔዎች ሕዝቡ መረጣቸው የተባሉትን የቀበሌ ሊቀመናብርት ላይ እምነት ስላጡ እነሱን አባረረው የካድሬነት እና የደህንነት ትምህርት ለወራት ያህል ሲሰጣቸው የነበሩ ግልገል ሹማምንቶች በየቀበሌ ገበሬ ማህበሩ የተመደቡ መሆኑን ያጋለጡት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ምንጮች ከዚህ በፊት ከነበረው የጉጥ አገዛዝ በአሁኑ ሰዓት በበለጠ ተጠናክሮ መቀጠሉን ያረጋግጣል ሲሉም ገልፀዋል::

ሕዝቡ የዕለት ኑሮ ከብዶት መላወሻ ባጣበት ወቅት ገበሬው በመዳበሪያ እዳ የስንግ ተይዞ መንቀሳቀሻ ባጣበት የግብር ክፍያ መክፈል አቅቶት እየተንገዳገደ ባለበት በዚህ ወቅት የቀድሞዎቹ ካድሬዎችን አባርረው እንደገና ሌላ የተራቡ የወያኔ ካድሬዎችን በደለበ ደመወዝ መሾማቸው አሳዛኝ ከመሆኑም በላይ አሳፋሪና ገደብ የለሽ የስልጣን ጥማት ያለባቸው መሆኑን በግልፅ የሚያሳይ ነው ሲሉ ድርጊቱን የተከታተሉት በርካታ ወገኖች ትዝብታቸውን እየገለፁ ይገኛሉ::

መላው የጠፋባቸው የወያኔ ባለስልጣናት ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ስብሰባ ላይ መቀመጣቸው የየዕለቱ ትልቁ ተግባራቸው ማድረጋቸውን ለወያኔ ጽህፈት ቤት ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገለፁ::

በስብሰባ መፍትሄ የሚገኝ እየመሰላቸው የወያኔ ቱባ ቱባ ባለሥልጣናት በየሄዱበት ስብሰባ እየተቀመጡ ያለ አንዳች ጥቅም ጊዜያቸውን እየደሉ ሲሆን፣ በዚህ ሳምንት ብቻ ሁለት ትላልቅ ስብሰባዎች አካሂደዋል:: በዚህም መሠረት ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓም ከጧቱ 3 ሰዓት እስከ 7 ሰዓት ድረስ አራት ኪሎ በሚገኘው በኢህአዴግ ቢሮ ውስጥ ተሰብስበው እንደነበር ምንጮቹ ገልፀዋል::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እንደምንጮቹ ገለፃ ከሆነ የወያኔ ከፍተኛ ባለሥልጣናት በአራት ኪሎ በሚገኘው የወያኔ ጽህፈት ቤት ውስጥ ለ4 ተከታታይ ሰዓታት በስብሰባ ያሳለፉ ሲሆን፣ ስብሰባውን በረከት ስምኦን የመራውና በርካታ የወያኔ ባለሥልጣናት በዚሁ ስብሰባ ላይ ተገኝተው እንደነበር አስረድተዋል::

እነ ተፈራ ዋልዋና ሌሎችም ከፍተኛ የወያኔ ባለስልጣናት በስብሰባው ላይ የተገኙ ሲሆን፣ በዚሁ ባደረጉት ስብሰባ ላይ በሚያዚያ ወር ውስጥ ስለሚደረገው ማሟያ፣ የቀበሌና የወረዳ ምርጫ በተመለከተ በረከት ስምኦን በአሁን ሰዓት የተደረገውንና እየተደረገ ያለውን ዝግጅት አስመልክቶ ለባለሥልጣናቱ ሪፖርት ያቀረበ ሲሆን፣ እነዚሁ ቱባ ቱባ ባለሥልጣናት ሞቃዲሾ ሳይወድ በግድ እንደ በረሐ እንጨት ማግደው እያስጨረሱት ስላለው ጦር አንዳችም ቃል ሳይተነፍሱ በቀጣዩ ምርጫ የተመለመሉት እና በማሟያ ምርጫ ወቅት ምክር ቤት ሊገቡ ይገባቸዋል ተብለው በበረከት የተመዘገቡትን ሰዎች ማንነት እና በፓርቲው ውስጥ ስላላቸው ድርሻ ጭምር ማብራሪያ ሰጥቷል:: በዚሁ በተደረገው ስብሰባ ላይ አንዱ የተነሳው ሐሳብ መራጭ ሕዝብ ባይኖር ምን መደረግ እንዳለበትም በዚሁ በምስጢራዊ ስብሰባ ላይ ሐሳብ ተሰጥቶበታል::

በ1997 ዓም በተደረገው ሐገር አቀፍ ምርጫ በዝረራ የተሸነፈውና ከጨዋታ ውጭ የሆኑት እነበረከት ስምኦን በግድና በኃይል ተመርጫለሁ በሚል ያለአንዳች ይሉኝታ የሰውን ልጅ እንደ እንስሳ በየመንገዱ እያስገደሉ ይህ ጠባሳ ከሕዝቡ አእምሮ ሳይጠፋ ዛሬ መልሰው ምርጫ ውጣ ማለት ከባድ መሆኑን የተነጋገሩበት የወያኔ ባለሥልጣናት ሁለት አይነት ዘዴ ማስቀመጥ እንደለባቸውም መክረዋል::

የመጀመሪያው በገንዘብ ኃይል ሲሆን፣ ሁለተኛው በግድና በማስፈራራት ውስጥ ውስጡን ቅስቀሳ በማካሄድ መሆኑንም ምንጮቹ ገልፀዋል:: በገንዘብ የተባለው ብዙ ብር ወጪ ተደርጐ የወያኔ ግልገል ሹማምንት በየሰፈሩ ታዋቂ የተባሉ ግለሰቦችን በገንዘብ ኃይል ሕዝብን እንዲያሳምኑላቸው ጥረት ማድረግ ሲሆን፣ ሁለተኛውና እንደ አማራጭ የተያዘው ሕዝቡ መምረጥ ግዴታ እንዳለበት ማሳሰብና አንዳንድ የማስፈራሪያ እርምጃ መውሰድ የሚሉ ይገኙበታል::

ልጁንና ቤተሰቡን በወያኔ ባለሥልጣናት ትዕዛዝ በቅልብ ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳዮች የተነጠቀው ሕዝብ ያለፈው ቁስል ጠገግ ሳይል እንደገና በግድ ወደ ምርጫ እንዲሳተፍ ይህንን ሕዝብ ማፈስራራት እያሉ የደሎቱት የወያኔ ሰው በላ ባለሥልጣናት ለፈፀሙት የሰው ልጅ እልቂት ቅንጣት ታክል ቅር ሳይላቸው አሁን ደግሞ እረደው፣ ፍለጠው የሚለውን አመረኔያዊ ትዕዛዝ ለመስጠት በድብቅ መዶለታቸው የእነዚህ ሰዎች ጤነኛ ነታቸው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው ሲሉ ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ሌላው በእለቱ የወያኔ ባለሥልጣናት በኢህአዴግ ጽሕፈት ቤት ውስጥ ባደረጉት ስብሰባ ላይ የተነሳው አጀንዳ የተጀመረው የኤች አር 2003 ሕግን መቀለበስ ስራ ተጠናቅሮ እንዲቀጥል የሚያሳስብ ሲሆን በዚህም የሚረዳ እጅግ ቁጥሩ የበዛ ገንዘብ ማለትም በሚሊዮኖች የሚቆጠር ብር ወጪ ተደርጐ እንዲመደብ ተወስኗል::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ከዚሁ ጋር በተጓዳኝ ሕዝብን ሊያሳምኑ ይችላሉ የተባሉ ታዋቂ ግለሰቦችም የዚሁ አካል ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ በስብሰባው ላይ የተወሰነ መሆኑና ለእነሱ መንቀሳቀሻ ጠቀም ያለ ገንዘብ እንደተመደበ የገለፁት የውስጥ አዋቂ ምንጮች ይህ ቡድን በሁለት የተከፈለ ሲሆን፣ አንደኛው ሐገር ውስጥ የሚሰራና ሁለተኛው ውጭ ሐገር እየተንቀሳቀሰ ተልዕኮውን የሚወጣ መሆኑንም ጨምረው አብራርተዋል።

በተመሳሳይ በወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ መሪነት የመከላከያ ከፍተኛ መኮንኖች የተሳተፉበት ስብሰባ በቤተመንግስት ውስጥ በሚስጢር ተካሂዶ እንደነበር የቤተመንግስት ምንጮችን ዋቢ ያደረገው ዘገባ ገልጿል።

እንደምንጮቹ ዘገባ ከሆነ ማክሰኞ እለት ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓም ከ11 ሰዓት ጀምሮ ምሽቱን ለብዙ ሰዓታት በተደረገው ምስጢራዊ ስብሰባ ሱማልያ የገባው የወያኔ ጦር ዙሪያ ያጠነጠነ ሲሆን ይህ ጦር የዛሬ ዓመት ወደ ሞቃዲሾ የገባው ጦርነቱ በአጭሩ ተጠናቆ እንደሚመለስ ተነግሮት የነበረ ቢሆንም እንደታሰበውና እንደታቀደው በአጭሩ ካለመቋጨቱም በላይ በጦሩ በደረሰው ከፍተኛ ኪሣራ ሞራሉ ከእለት ወደ እለት እየላሸቀ መሆኑን አፅንኦት ሰጥተው እንደተወያዩበትም አስረድተዋል። በዚህም የተነሳ ሞቃዲሾ ዘምቶ ያለውን ጦር ወደ ኋላ ወረዳ ለማውጣት ሐሳቡ የተነሳ ቢሆንም ጦሩ ሲዘምት በተሰጠው የተሳሳተ መረጃ እና በየቀኑ በሚደርስበት ከፍተኛ ጉዳት የተነሳ ያኮረፈ ስለሆነ ሊያምፅ ይችላል ስለዚህ ወደኋላ ወረዳ እንደወጣ ትጥቁን እንዲፈታ ማድረግ ይሻላል ተብሎ ሐሳብ የተነሳ ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ መስዋዕትነት የከፈለውን ጦር ትጥቅ ካስፈታነው ከኋላ ያለው ጦር ይህንን ከሰማ «ነገ በእኔም ላይ ይህ እርምጃ ሊወሰድብኝ ይችላል» በሚል ጦሩ ሊያምፅ ስለሚችል ይህ ሐሳብ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይችል እርስ በእርሳቸው ተማምነው በሁለቱም ሐሳብ ሳይስማሙ ስብሰባው እንደተጠናቀቀ የቤተመንግስት ምንጮች አረጋግጠዋል።

ከአሁን አሁን ጦርነቱ ተጀመረ ተብሎ በስጋትና በውጥረት ላይ ያለው የድንበሩ ችግር ሁለቱም ቡድኖች የማሻሻያ እርምጃ እንዲወስዱ ማሳሰቢያ በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮንዶሊዛ ራይስ ቢሰጥም የየበኩላቸውን ዝግጅት አጠናክረው እንደቀጠሉበት ከተለያዩ አካባቢዎች የሚደርሱን ዘገባዎች ያስረዳሉ።

የሻዕቢያው ሊቀመንበር ኢሳያስ አፈወርቂ ሰሞኑን ይህንኑ የጦርነት ዝግጅት ከሚያደርገው እንቅስቃሴ በተጨማሪ ከሱዳንና ከሊቢያ ጋር ወታደራዊ ስምምነት መፈራረሙ ታውቋል። በዚሁ ወታደራዊ ስምምነት ውስጥ መኮንኖችን ለማሰልጠንና ትምህርት ነክ ላይ በሚል ውጫዊ ሽፋን የተፈራረሙ ቢሆንም ውስጥ አዋቂ ዲፕሎማቲክ ምንጮች እንደሚሉት ግን ከሊቢያ ወደ ሱዳን ገብቶ ከሱዳን ወደ ኤርትራ በድብቅ የጦር መሣሪያ ልገሳ እንደተፈፀመላቸው እና አሁንም እገዛው እንደሚቀጥል ያመለክታል ሲሉ ገልፀዋል።

በወያኔ በኩልም ቢሆን የጦርነት ዝግጅቱ ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን፣ በወታደራዊ ሙያ የሰለጠኑ ወታደሮችን ከየካምፑ በማውጣት እስከ ግንባር ማሰማራት ጀምሮ ሌሎች ሙያዎችን እስከ ማሰልጠን የደረሰ ሲሆን፣ ሰሞኑንም በተለያዩ ጊዜያት በአዋሽ አርባ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ የካድሬነት ትምህርት ሲከታተሉ የነበሩት መኮንኖች



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ተመርቀው ወደ ጦር ክፍሉ ተደልድለው የጦርነቱን መጀመር በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ ሲሉ የመከላከያ ምንጮቻችን አብራርተዋል::

የወያኔ ጦር በአሁን ሰዓት በአምስት ዕዞችና በ28 ክፍለ ጦሮች እንዲሁም ከ112 ሻለቃዎች በላይ ተደራጅቶ ዕልቂቱን በመጠባበቅ ላይ ያለ ሲሆን፣ በተለይም ከንድ መሪ እስከ ዕዝ አዛዥ ድረስ በሕወሓት ሰዎች ተወጥሮ ጦሩ የውጊያው መጀመርን እየተጠባበቀ እንደሚገኝ የመከላከያ ምንጮች አጋልጠዋል::

በአሁን ሰዓት የጦርነቱን መጀመር በመጠባበቅ ላይ ያለው ጦር በአዲስ መልክ እንዲዋቀር ተደርጐ አምስቱ እዞች በሕወሓት ጄኔራሎች እንዲመራ፣ አየር ኃይሉ በሕወሓት ጄኔራሎች እንዲተዳደር፣ ከ28 ክፍለ ጦሮች ውስጥ 27 ያህሉ በሕወሓት ኮሎኔል ማዕረግ ባላቸው ሰዎች እንዲተዳደርና 112 ሻለቆችም ከ75 ፐርስንት በላይ በሕወሓት መኮንኖች እንዲመሩ ተደርጐ ተዋቅሯል ሲሉም ምንጮቹ ገልፀዋል::

በውጊያ ወቅት ጦሩ ወደ ኋላ እንዳያፈገፍግም መቺ ኃይል ተዘጋጅቶ በመጠባበቅ ላይ መሆኑን የገለፁት ምንጮች በጦሩ ውስጥ ባለው የሕወሓት የበላይነት የተነሳ ሌሎች አንጋፋ ብሔሮች በተለይ ኦሮሞ እና የአማራ ተወላጅ መኮንኖች በየጊዜው ቅሬታ ቢያቀርቡም ምላሹ እስራትና ወከባ መሆኑን በመረዳታቸው ውስጥ ውስጡን እያልጐመጐሙ ይገኛል ብለዋል:: ጦሩም እንዳይንሸራተትና ክፍተት እንዳይፈጥር ለማድረግ በሚል ሰንካላ ምክንያት የሕወሓት መኮንኖች በሙሉ ቁልፍ ቁልፍ ቦታውን እንዲቆጣጠሩ ተደርጓል ሲሉም ጨምረው አስረድተዋል::

በሱማሌ ውስጥም የዘመተው የወያኔ ተላላኪ ጦር ጦርነቱ አይመለከተኝም በማለት ማቆም ሲገባው በማይመለከተው ጦርነት ውስጥ ተዘፍቆ አይኑ እያየ በየቀኑ እያለቀ ይገኛል:: በተለይም በዚህ ባሳለፍነው ሳምንት በወያኔ ጦር ላይ የተፈፀመው ዘግናኝ እልቂት ከመቼውም ጊዜ በላይ የከረረና የገዘፈ መሆኑን አለም አቀፍ ሚዲያዎች አጋልጠዋል:: ከሞቃዲሾ ወጣ ያሉትንም አካባቢዎች ቢሆን መልሶ የእስላማዊ ሕብረቱ እየተቆጣጠረና የሽግግር መንግስትቱ ጦርና ሌሎቹንም እያሳደደ ይገኛል:: በሞቃዲሾም የበላይነት አገኛለሁ እያለ የሚፍጨረጨረው የወያኔ ጦርም በየዕለቱ በሚደርስበት ከፍተኛ ጥቃት እያለቀ ይገኛል:: ይህ በሆነበትና በኦጋዴን አካባቢም ከፍተኛ ጥቃት እየደረሰበት የታጣቂ ኃይሎች በሚሰነዝሩት ጥቃት የተነሳ የወያኔ ጦር መግቢያ መውጪያ ጠፍቶት አንዴ ወደ ሻላቦ ሌላ ጊዜ ወደ ደገሐቡር እየተሯሯጠ እንደሚገኝ የጠቆሙት የመከላከያ ምንጮች ይህ ሁሉ መከራ በጦሩ ላይ ሲፈፀምበት እያዩ የወያኔ ባለሥልጣናት ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሀብት ዘረፋና ንጥቂያ እያካሄዱ መሆኑ የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ወራዳ ተግባር ነው ሲሉ ምንጮቹ በቁጭት ይገልፃሉ::

በተያያዘ ዜና በቀድሞ የራሽያ ግዛት ቤላሩስ ለአየር ኃይል ትምህርት ለመከታተል ከሄዱት መኮንኖች መካከል 6 ያህሉ በዚያው ቤላሩስ ጥገኝነት መጠየቃቸውን ከመከላከያ ምንጮቻችን የተገኘው ጥቆማ ገለፀ::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እንደምንጮቹ ገለፃ ከሆነ ከ6ወር በፊት ለትምህርት የተላኩት የአየር ኃይል መኮንኖች የተላኩበትን የቴክኒክ ትምህርት አጠናቅቀው ወደ ሐገር ውስጥ ሊመለሱ በዝግጅት ላይ እንዳሉ 6 ያህሉ «መመለስ አንፈልግም፣ ዘረኛና የአንድ ወገን የበላይነት ያነገሰ ቡድንን አናገለግልም» በማለት በዚያው በቤላሩስ ጥገኝነት የጠየቁ ቢሆንም ቤላሩስ እና የወያኔ ቡድን ባላቸው ምስጢራዊ ግንኙነት ጥያቄያቸው ተቀባይነት ማጣቱን ገልፀዋል::

ምንጮቹ አክለውም የቤላሩስ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ከወያኔ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ጋር እየተነጋገረበት ያለ ሲሆን፣ በተለይም ጥገኝነት ጥያቄ ያቀረቡት ተላልፈው እንዲሰጧቸው የወያኔ ባለሥልጣናት ተደጋጋሚ ጥያቄ እያቀረቡ ቢሆንም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የቤላሩስ ባለሥልጣናት ምላሽ እንዳልሰጧቸው ታውቋል ሲሉ እነዚሁ ምንጮች ጠቁመዋል::

ምናልባትም በቅርቡ ወደ ሌላ ሐገር እንዲሄዱ ሊያመቻቹላቸው ይችላል ያሉት ምንጮች ወደ ሐገር ውስጥ ተላልፈው ከተሰጡ የሚደርስባቸው ድብደባና ሌላም ሌላ ችግር ከወዲሁ እጅግ ዘግናኝ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ሲሉም ያላቸውን ስጋት ገልፀው በአሁን ሰዓት የጦርነት ነጋሪት እየተጐሰመ ባለበት በዚህ ወቅት ላይ ነባርና ልምድ ያላቸው መኮንኖች ጥገኝነት መጠየቃቸው ለወያኔ ቡድን ትልቅ የራስ ምታት እንደሆነበትም ለማወቅ ተችሏል ሲሉ ምንጮቹ አትተዋል::

የብሔር ብሔረሰብ ቀን በሚል ወያኔ የፈጠረውን በዓል ለማክበር ከጅጅጋ ወደ አዋሳ ይጓዝ የነበረ የወያኔ ተላላኪ ግለሰብ በመኪና አደጋ ሕይወቱ ሊያልፍ እንደቻለ ተገለፀ::

ሐሙስ ሕዳር 26 ቀን 2000 ዓም በዓሉን ለማክበር ይጓዝ የነበረው ይኸው የወያኔ ተላላኪ ግለሰብ በድንገተኛ ሁኔታ ሲያሽከረክራት የነበረችው መኪና በመገልበጧ ሕይወቱ ሊያልፍ እንደቻለ ታውቋል::

በፌዴሬሽን ምክር ቤት የሱማሌ ክልል ተጠሪ የሆነው ይኸው ግለሰብ ለወያኔዎች ተላላኪ በመሆን የሱማሌን ሕዝብ መልሶ እየረገጠና እያስረገጠ ከክልሉ ፕሬዝዳንት ጋር በመሆን ሕዝብን የበደለ መሆኑን የገለፁት ከተማ ነዋሪዎች ግለሰቡ ለስራ ጉዳይ በተሰጠው መኪና እንደፈለገው ሲዝናናበት የነበረ ሲሆን፣ አሁንም ወደ አዋሳ ሕዳር 29 ቀን በዓል ለማክበር በጉዞ ላይ እንዳለ ተገልብጦ ሕይወቱ ማለፉን ምንጮቹ ገልፀዋል::

ወያኔ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም እንዲያመቻቸው እና ሕዝብን ለማታለል ይረዳው ዘንድ በየጊዜው አዳዲስ ስልቶችን እየነደፈ ሲንቀሳቀስ የቆየ ቡድን ሲሆን፣ አሁንም የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በሚል ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጐ ባለሥልጣናቱ ሲዝናኑ እንደነበረ ለማወቅ ተችሏል::

የወያኔ ባለሥልጥናት በየጊዜው በሐገር ሐብትና በሕዝብ ንብረት እንደልባቸው ከሐገር ሐገር እየተዝናኑ መልሰው ይህንኑ ሕዝብ በጠመንጃ ኃይል ለመግዛት ያላሰለሰ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ከሰሞኑም የወያኔ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ወርቅነህ ገበየሁ እና የማረሚያ ቤቱ ምክትል ኮሚሽነር ወዲ ሻምበል በጋራ በመሆን የፖሊስ ልብሶችንና ትጥቆችን ለመሸመት ወደ ቻይና እና ጣሊያን ሐገሮች ማቅናታቸው ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ዘገባ ያስረዳል።

እነዚሁ ሁለት ቱባ ባለሥልጣናት በሐገር ውስጥ ያሉት የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ጥራት የላቸውም በሚል ሰበብ ወደ ቻይና ጣሊያንና ሌሎች ሐገሮች የፖሊስ ልብሶችን ለመሸመት እየተዟዟሩ መሆኑን የገለፀው የምንጮቹ ዘገባ በተለይም በአሁን ሰዓት በሐገሪቱ ውስጥ በፌዴራል ደረጃ ሶስት አይነት ፖሊስ ያለ ሲሆን፣ እሱም የፌዴራል ፖሊስ፣ የማረሚያ ቤት ፖሊስ እና የአዲስ አበባ ፖሊስ በሚል የተከፋፈለ መሆኑን ገልፀዋል።

ለዚህም ሲባል የፌዴራል ፖሊስ ልብስና ሌሎችንም ትጥቆች ኮሚሽነር ወርቅነህ ገበየሁ እንዲገዛ፣ የአዲስ አበባውን ፖሊስና የወህኒ ቤት ፖሊስ ልብሶችን ደግሞ ወዲ ሻምበል እንዲገዛ ሁለቱንም አንድ ላይ ተጣምረው የተላኩ ሲሆን፣ በሐገር ውስጥ ያሉትን የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ማበረታታት ሲገባቸው ጠቀም ያለ ኮሚሽን ከውጭ ሐገር ካምፓኒዎች ለማግኘት ሲሉ ብቻ እጅግ ከፍተኛ ወጪ ተደርጐ ሶሰትና አራት ሐገራት እየተዟዟሩ መሆኑንም ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ለራሳቸው ኮሚሽን ጠቀም ያለ ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ብቻ ወደ ውጭ ሐገር ተሯሩጠው የወጡት ሁለቱ የወያኔ ባለሥልጣናት በፖሊስ ሠራዊት ላይ መጠን የለሽ በደል እየፈፀሙበት እንደነበርና በተለይ ሁለቱም ጥገኛ ከመሆናቸው አንፃር ያላቸውን ስልጣን በበታቾቻቸው ላይ የሚጠቀሙበት መሆናቸውን ምንጮቹ ገልፀው ወርቅነህ ገበየሁ የድል አጥቢያ አርበኛ ሆኖ እራሱን ያቀረበ የተላላኪው የኦህዴድ አባል ሲሆን ወዲ ሻምበል የተባለውም ግለሰብ ዘር ከልጋም ይሳባል እንዲሉ በአባቱ ኦሮሞ በእናቱ ትግሬ ቢሆንም የዘመኑ የዘር ሐረግ በልጦበት የሕወሓት አባል በመሆን በረሐ የነበረና እዚያም እያለ ስንት ንፁሀን ዜጐችን በእስርና በቅጣት ሲያሰቃይ የኖረ መሆኑንም ምንጮቹ አጋልጠዋል።

በተመሳሳይ የጦሩን ወታደራዊ ልብስ ለብዙ አመታት ሲያቀርብ የነበረው የወያኔ ካምፓኒ የሆነው አልመዳ ጨርቃጨርቅ የምርት ጥራቱ ቀንሷል በሚል ከአንድ ቻይና ኩባንያ እንዲገዛ በጄኔራል ሳሞራ የኑስ መታዘዙን የመከላከያ ምንጮቹ ገለፁ።

ከዚህ በፊት ለ10 ዓመታት ያላነሰ ጊዜ ከዚህ ከሕወሓቱ ኩባንያ ሲገዛ የቆየ ሲሆን፣ አሁን በድንገት ከውጭ ሐገር መገዛት አለበት ብለው እነ ሳሞራ የኑስ ትዕዛዝ መስጠታቸው ከሐገር ውስጥ ካለው ድርጅት ምንም አይነት ኮሚሽን የማይገኝ በመሆኑ ከ3 መቶ ሺህ ለማንያንሰው ጦር ልብስ ለመሸመት ፊታቸውን ወደ ቻይና ያዞሩት እነ ሳሞራ የኑስ በነበራቸው ሐብት ላይ እንደገና ሌላ ሐበት ለማከማቸት አጭሩ መንገድ ይኸው መሆኑን በመረዳታቸው ግዥው እንዲከናወን ትዕዛዝ መስጠታቸውንም አጋልጠዋል።

ዛሬ መላው የሐገሪቱ ሕዝብ በኑሮ ውድነት እጅግ ተቸግሮ ባለበት ሰዓት ወያኔ የአገዛዝ እድሜዬን ያስረዝሙልኛል በሚል ብቻ ለጦሩና ለፖሊስ ሠራዊት ልብስና ትጥቅ ለመሸመት መሯሯጡ ትዝብት ላይ የሚጥለው ከመሆኑም በላይ ጦሩም ሆነ ፖሊሱ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ከሕዝብ አብራክ የወጡ መሆኑን በመዘንጋት ያለ አንዳች ይሉኝታ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ አድርጎ ግዥ መፈፀሙ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባውን ነገር ጠንቅቆ ካለማወቅና ሕዝብ ምን ያመጣል በሚል ንቀት የፈፀሙት መሆኑን ምንጮች ጨምረው ገልፀዋል::

በአሁን ሰዓት ወያኔ በምስራቅ ኢትዮጵያ ኦጋዴን፣ በሰሜን እንዲሁም በሱማሌ ሞቃዲሾ በገጠመው ችግር ጦሩን በትኖ መሐል ሐገር ሕዝቡን ሊያስፈራራበት የሚችል በቂ ኃይል በማጣቱ በተለያዩ ማሰልጠኛ ካምፖች ውስጥ ፖሊስ ባልደረቦችን እያሰለጠነ ይገኛል::

ሰሞኑን በለገዳዲ ለ5ወራት ያህል የፖሊስ ትምህርት ሲከታተሉ የቆዩት ከ3ሺህ የማያንሱ ፖሊሶች የተመረቁ ሲሆን፣ እነዚህ ፖሊሶች በኦሮሚያ ክልል ባሉ ከተሞች በነቀምት፣ በጅማ፣ በአምቦ፣ በባሌ፣ በሐረር፣ እና በሌሎችም ዋና ዋና በሚባሉ ከተሞች ተበትነው ሥራቸውን እንደሚጀምሩ ታውቋል::

ወያኔ በተለያዩ አካባቢዎች በደረሰበት ከፍተኛ አጣቢቂኝ የተነሳ ጦሩን በየቦታው በትኖ ያለ ሲሆን፣ ከሰሜን ግንባር ቀጥሎ በሞቃዲሾ ብቻ ከ30 ሺህ በላይ ጦር ማስፈሩን የመከላከያ ምንጮች ገልፀው በኦጋዴንም እንደዚሁ ከ20ሺ በላይ ሠራዊት መሠማራቱን አስረድተዋል::

የወያኔ ባለሥልጣናት ዙሪያውን በተከሰተባቸው ችግር ምክንያት ጦሩን እንደ ክረምት ዘር በየቦታው በትነው መሐል ከተሞች ባዶ ስለሆኑባቸው ሥጋት ውስጥ ስለገቡ ለጊዜው መሸፈኛ በሚል የፖሊስ ሰራዊት በ 5 ወራት ስልጠና እያስመረቁ በየከተማው በመመደብ ላይ ያሉ ሲሆን፣ አሁንም በእነዚህ ፖሊሶች ስልላተደሰቱ በድብቅ አንድ ተወርዋሪ ብርጌድ በሁርሶ ለማሰልጠን እቅድ መውጣቱን ለፌዴራል ፖሊስ ቅርበት ያላቸው ወገኖች አጋልጠዋል::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com